

# የልደታ ክ/ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት

# የዜጎች ስምምነት ሰነድ

ሀምሌ 2015 ዓ/ም

## መግቢያ

የልደታ ክ/ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት በከተማ አስተዳደሩ የተሰጠውን ተልዕኮ በማሳካት ረገድ ባለፉት ዓመታት በከተማዋ ስር ሰዶ የቆየውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በዘላቂነት በመቅረፍ ፈጣንና ፍትሃዊ ልማት ለማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ግንባታ ያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ጅምር ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡
ሆኖም ግን ጽ/ቤቱ በነበረው አደረጃጀት ጥራት ያለው የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ግንባታ በማካሄድ ለከተማችን ነዋሪ በሚፈለገው ጊዜ ተደራሽ ማድረግ ያልቻለ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 74/2014 የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በሚል በአዲስ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ በአዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ የፕሮጀክት ዝግጅት፤ ስታንዳርድ ዝግጅት፤ ክትትልና ቁጥጥር፤ የኮንትራት አስተዳደር እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት፤ ክትትልና ቀጥጥር የሚሉት በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በመሆኑም የልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር የሚያከናውናቸውን የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታዎች ዕቅድና የአገልግሎት ስታንዳርድ የያዘ የዜጎች ስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

# ራዕይ /Vision/

አዲስ አበባ ከተማን በ2017 ዓ/ም ከተማዋን የሚመጥኑ የህዝቡን ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ ዲዛይኖችን በማዘጋጀት የመንግስት ህንጻዎችን ገንብቶ ለነዋሪዎቿ ተደራሽ ማድረግ፡፡

# ተልዕኮ /Mission/

አዲስ አበባ ከተማን ስታንዳርዱን በጠበቀ ወጪ ቆጣቢ ዲዛይን መሰረት የመንግስት ህንጻዎችን ገንብቶ ተደራሽ በማድረግ ለከተማዋ ነዋሪዎች ምቹ እና ጥራ ያለው አገልግሎት መስጠት፡፡

# ዕሴቶች /Values/

ግልጽነት!

ተጠያቂነት!
ፍትሃዊነት!
ለለውጥ ዝግጁነት!
ጥራትና ወጭ ቆጣቢነት!
ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት!
ቅድሚያ ለደህንነት (Safety First)!

## የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት

## ስትራቴጂያዊ ውጤቶች

## (Strategic Results)

- ስታንዳርዱን ጠብቆ የተዘጋጀ የግንባታ ዲዛይን፣ የስራ ተቋራጭና የአማካሪ ግዢ፤
- በተገነቡ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ኅብረተሰቡ የሚፈልገውን ግልጋሎት ተጠቃሚና ተደራሽ ይሆናል፤
- የመንግስት ተቋማት ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ያደርጋል፤

## የዜጎች ስምምነት ሰነዱ ዓላማ

- ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የከተማዋን የህዝብ ቁጥር ታሳቢ በማድረግ ለቀጣይ ሁለት የስትራተጂክ ዘመናት ሊኖር የሚችለውን የህዝብ ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህንን ሊሸከም የሚችል የማህበራዊ ተቋማት ለመገንባት፤

- በከተማዋ የሚገነቡ ግንባታዎች በጊዜ፣ በጥራትና በወጪ ቆጣቢነት ከመገንባት ባሻገር ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ደረጃውን የጠበቀ የግንባታ ግብዓት ፍተሻ ለማድርግ፤ ተቋማት ከግንባታ ፍላጎት መለየት ጀምሮ በግንባታ ሂደትና በርክክብ ወቅት የሚጠበቅባቸውን በግልጽ በማስቀመጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ከመከሰታቸው በፊት በማረም ስራን ለማቀላጠፍ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

## የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባራት

1. የግንባታውን ኢንዱስትሪ ለማዘመን የሚያስችሉ በዲዛይን፣ በኮንስትራክሽን ግብዓትና ግንባታ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን ያጠናል፤ ሲፈቀድም ይተገብራል፤
2. በግንባታው ዘርፍ የተሰማሩ የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን አቅም ይገነባል፤
3. የግንባታ ግብዓትና የጉልበት የገበያ ዋጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማጥናት የዋጋ ተመን ያወጣል፤ ሲጸድቅ ለዘርፉ ተጠቃሚ አካላት ያሰራጫል፤

4. በግንባታና ዲዛይን እና የግንባታ ግብአት ማምረት ላይ የሚሳተፉ የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ ግብዓት አምራችና አቅራቢዎችን፣ የግንባታ መሳሪያ አከራዮችን ይመዘግባል፤ የሙያና የብቃት ማረገገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይሰርዛል፤ ዕድሳት ያደርጋል፤ ህጋዊ ፈቃድ ይዘው መስራታቸውን ያረጋግጣል፤

5. የግንባታ ግብዓት ናሙናዎችን ከማምረቻ ቦታዎች፣ ግንባታ ከሚከናወንባቸው አካባቢዎች ናሙና በመውሰድ በላቦራቶሪ ጥራታቸውን ያረጋግጣል፤ ችግር በታየባቸው ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ በተጠየቀ ጊዜ ከሌሎች ተቋማትና ግለሰቦች አስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል የግንባታ ግብዓት የጥራት ምርመራ ያካሂዳል፤ ውጤቱን ያሳውቃል፤

6. የዲዛይንና ግንባታ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ሲጸድቅም መተግበራቸውን ይከታታላል፤ ይቆጣጠራል፤

7. የግንባታ ግብዓት ሀብት ጥናት አቅም ያጠናል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤

8. በግንባታው ዘርፍ ከውል ጋር የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በስምምነት እንዲፈቱ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

9. የኮንስትራክሽን ዘርፍ የመረጃ መረብና ማዕከል እንዲኖር ያደርጋል፤ መረጃዎችን ይመዘግባል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤

10. ለግንባታ የሚከፈሉና የተከፈሉ ክፍያዎችን እና የተከናወኑ የግንባታ ሥራዎች ህጋዊነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን ኦዲት ያስደርጋል፤ በግኝቱ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

11. ማንኛውንም የአስተዳደሩ የህንጻና ተመሳሳይ የግንባታ ስራዎችን የከተማ አስተዳደሩን ወክሎ አግባብ ባለውህግ መሰረት ውል ይፈጽማል፤ ኮንትራት ያስተዳድራል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅም በውሉ መሠረት መከናወኑን ተቆጣጥሮ ይረከባል፤ ህንጻው ወይም ግንባታው ለተከናወነለት ተቋም በሰነድ ያስረክባል፤

12. የህዝብ መጸዳጃ ቤት እንዲገነባ ያደርጋል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለተፋሰስና አረንጓዴ አካበቢዎች ልማት ኤጀንሲ ያስተላልፋል።

| ተ/ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | የሚወስደው ሰዓት |
|---|---|---|
| 1 | *የፀደቀን የጨረታ ሰነድ ለተቋራጭና አማካሪ መሸጥ* | 30 ደቂቃ |
| 2 | *የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ ማብራሪያ ለሚፈልጉ ተጫራቾች ማብራሪያ መስጠት* | 1 ሰዓት |
| 3 | *ተጫራቾች በቴክኒክና ፋይናንሻል ግምገማ ውጤት ላይ ቅሬታ ካቀረቡ ምላሽ መስጠት* | 2 ሰዓት |
| 4 | *አማካሪ ድርጅት፣ ሰርቪየር እና የመጨረሻ ተጠቃሚ ተቋም በተገኙበት ከስራ ተቋራጩ ጋር በቼክሊስት መሰረት የሳይት ርክክብ ማድረግ* | 4 ሰዓት |
| 5 | *ፕሮጀክቶች በውለታ ላይ በተቀመጠው ጥራት፣ የጊዜ ሰሌዳና የውለታ ዋጋ መሰረት እየተከናወኑ መሆኑን መከታተል* | 4 ሰዓት |
| 6 | *የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ከአማካሪ ጋር በጋራ በቃለ ጉባዔ አስደግፎ መገምገም፣ ሪፖርት ማቅረብ* | 3 ሰዓት |
| 7 | *የአማካሪና የስራ ተቋራጭ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ መቀበልና ተገቢነቱን ማረጋገጥ* | 3 ሰዓት |
| 8 | *የግንባታ ስራው በውሉ መሰረት በጥራት መሰራቱን በማረጋገጥ ጊዜያዊ የመረካከቢያ ሰነድ በማዘጋጀት የመጀመሪያ ርክክብ መፈጸም* | 8 ሰዓት |
| 9 | *የመጀመሪያ ርክክብ ከተፈጸመ ከ1 ዓመት በኋላ ግንባታው የሚስተካከል ስራ ካለው እንዲታረም ማድረግ* | 8 ሰዓት |
| 10 | *የመጨረሻ ክፍያን በውለታው መሰረት አስልቶ ማቅረብ* | 16 ሰዓት |
| 11 | *ከተቋራጭ ጋር የመጨረሻ ርክክብ መፈጸም* | 4 ሰዓት |
| 12 | *በስራ ተቋራጩና በአማካሪው የውለታ ሰነድ ላይ የተጣሱ ህጎች ሲኖሩ በሚመለከተው አካል እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ* | 2 ሰዓት |
| 13 | *የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት ለሚሰራላቸው ፕሮጀክቶች ፕላን ስምምነት እንዲያቀርቡ መጠየቅና ክትትል ማድረግ* | 2 ሰዓት |
| 14 | *በሚመለከተው ባለድርሻ አካለት ረቂቅ የፕሮጀክት የአዋጭነት ሰነዱን ማስተቸት* | 4 ሰዓት |

| | | |
|---|---|---|
| 15 | *የተዘጋጀውን የመጨረሻ ዲዛይን /Final Design/ በሌሎች ባለሙያዎች እና ጥያቄ አቅራቢያው ተቋም በተገኙበት ማስገምገም* | 4 ሰዓት |
| 16 | *ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ /Variation Order/ እና ሌሎች ከውለታ ሰነድና ዲዛይን /Drawing/ ላይ የሌሉ የግንባታ ስራዎች Excuted Works/ በአግባቡ መጠናቀቅቸውን የመስክ ምርመራ እና ልኬቶችን መውሰድ* | 8 ሰዓት |
| 17 | *ከTake off, BOQ & Grand Summery ላይ ልዩነት የተፈጠረባቸውንና በመስክ ምልከታ የተገኙ ግኝቶች ላይ ከስራ ተቋራጩ ጋር መተማመን ላይ መድረስና የፕሮጀክቱን የመጨረሻ ክፍያ ኦዲት ሪፖርት ማተናቀቅ* | 24 ሰዓት |

